EthioLion

# አልታየን አለ

ትውልድ እያለፈ ፤ ትውልድ እየተካን
አንድ ቀን ሳይደላን ፤ ሁሌ እንደተገፋን
ታሽን ተወቀጥን ፤ እንደ ቁርበት ፤ ለፋን
አቃለሉ ጣሉን ፤ ተናቅን ፤ ተተፋን
የደላን ይመስል ፤ ቅንጣትም አልከፋን
በየፊና መሮጥ ፤ ከምድር እስኪያጠፋን
መባነን አልቻልንም ፤ ጥንብ እየከረፋን ።

አሰሩ አሰቃዩ ፤ ገደሉ መተሩን
ታሪክን አጠፉ ፤ አቃጠሉ ደብሩን
ከትውልድ ስፍራችን ፤ ነቅለው አባርሩን
ሸጡት ሸነሸኑት ፤ በሃራጅ አገሩን
ለዘራፊ ሰጡን ፤ ከፋፈቱት በሩን
ስንቴ እንሞታለን ፤ ከነነፍስ ሲቀብሩን ።

ከንሰሳት ካራዊት ፤ አነስን አልተሻልን
ካገር ተባረርን ፤ ከርስት ተነቀልን
ቤቱን በላያችን ፤ናዱ አፈረሱልን
ለህንድና ለአረብ ፤ አገሩን ሸጡልን
ጠምደው አረሱብን ፤ በግፍ ተሰቀልን
ጀግንነት የት ገባ ፤ ብዙ የተባለልን
ምነው እናታችን ፤ ወንድ አትወልድልን ?

የአረብ የቻይና ፤ ምስለኔ ቅጥረኛ
ባንዳ ፤ የባንዳ ልጅ ፤ የሞት መላከተኛ
አገሩን በካዳ ፤ ልበ ሙቅ ፤ ምንደኛ
ኢትዮጵያ ስላልን ፤ ሆነን ወንጀለኛ
በጠላት ተቀጥሮ ፤ ሲያረገን እስረኛ
ምነው መሽቶ ቀረ ፤ አልነጋ አለ ለኛ
መቆጨት ተስኖን ፤ ተጠቃን ከፉኛ ።

የመከራው ብዛት ፤ አላባራ እያለ
ጫንቃው ካልከበደው ፤ እየተበደለ
በዘር በሃይማኖት ፤ ከተከፋፈለ
አለሁ አይባልም ፤ በቁም ሞቶ ሳለ ።
ዛሬስ አሻፈረኝ ፤ ማለት ካልተቻለ
በህብረት ተነስተን ፤ ትግል ካልቀጠለ
ትላንት ተመስግኖ ፤ ነገ ይብስ የለ
ምን አዚም ፤ ጋረደን ፤ አልታየን አለ ?።

ታዛቢው ... March 11, 2012

EthioLion.Com

Ethiopia Will Prevail!